# "የዲሞክራሲ መሠረቶች በኢትዮጵያ"
# "የዓላማ አንድነት ለድል ወሳኝ ነው"
# በቅርቡ በገበያ ላይ የዋለ መጸሐፍ ግምገማ

## ደራሲው፤ ታምራት ቢ ስመኝ

ደራሲው በመጀመሪያው ገጽ መግቢያ ላይ እንዲህ በማለት ጽሁፋቸውን ይጀምራሉ፤ "የኢትዮጵያ ኢሊት የፖለቲካ መሪዎችና በዲያስፖራ የሚገኙ ደጋፊዎቻቸው ለኢህደግ ፖለቲካ ወጥመድ መሣሪያ በመሆን ብዙ መስዋዕት የተከፈለበትንና፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ፤ ነፃነት፤ ፍትሕና ርትዕ፤ አንድነትና ዲሞክራሲያዊ እኩልነት የቆመውን የቅንጅት ተቋዋም ሲያፈራርሱ ይታያል። ካለፈው የፖለቲካ ክስረት ለመማር ያልቻለው ይህ ክፍል ኢትዮጵያ የምትፈልገው ለመላው ሕዝብ ጥቅም መቆምን፤ እውነትን ሐቀኝነትንና የዲሞክራሲ ባሕልን ሥራ ላይ ማዋልን እንጂ ራስን ማገልገልና፤ ሥልጣን መሻማትን አልነበረም።"

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደሚቻለው ደራሲው መጽሀፉን የጻፉት የቅንጅት መሪዎች ከእሥር እንደተፈቱና በመሀከላቸው የተፈጠረው ልዩነት በይፋ እንደወጣ መሆኑን ለማወቅ ይቻላል። ይህ ወቅት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገራችን ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በቅንጅት ፓርቲ መሪነት ተከስቶ የነበረው ተስፋ ሰጭ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ በመሪዎቹ መሀከል በተፈጠረው አነስተኛ ቅራኔ የተነሳ ወደሁዋላ እንዲጎተት በመደረጉ ክፉኛ ያዘንበት ጊዜ ነበር። ደራሲው ይህንን ወቅታዊ ሁኔታ ተመርኩዘው በሀገራችን ላይ የደረሰውን አስከፊ የፖለቲካል የሶሻልና የኤኮኖሚ ይዞታ በልዩ ልዩ አንፃር በመመልከት ትንታኔ በማቅረብ ለሀገር ደህንነት፤ ለህዝባችን ጠቀሜታ ይበጃል የሚሉትን በጠራና ማንም ወገን አንብቦ በቀላሉ ሊረዳ በሚችለው ቋዋንቋዋ መጽሀፉን አዘጋጅተዋል። ህትመቱ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ታትሞ ገበያ ላይ ውሎአል።

መጽሃፉ በሰባት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፋፈል ሲሆን በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥም በርካታ ንኡስ አርዕስቶች ላይ ጥልቀት ያላቸው ትንታኔዎች ተካተዋል። የሀገራችን ዋነኛና መሠረታዊው ችግር ለዘመናት ተንሠራፍቶ የኖረውና አሁን ደግሞ በአስከፊና የሀገራችንን ሕልውና በሚያጠፋ መልኩ በወያኔ አገዛዝ አማካኝነት እየተገፋበት ያለውን የጥፋት አስተዳደር ደራሲው የጽሁፋቸው መነሻ መሆኑን አበክረው ያስረዳሉ። ይህም ችግር ዘርፈ ብዙና በወቅቱ ካልተቀጨ ውጤቱ በሕዝባችን ላይ ሊያስከትል የሚችለውና በአሁኑ ወቅትም የሚታየው የረሀብ፤ የቸነፈር የርስ በርስ እልቂት፤ የበሽታና የጥፋት ሁኔታ የማይቀር መሆኑን በዝርዝር ያስረዳሉ።

የመጀመሪያው ምዕራፍ በሕዝብ ያልተወከለ መንግሥት ሊያስከትል ስለሚችለው ጥፋት በሰፊው ይተነትናል። ደራሲው ስለ መልካም አስተዳደር ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፤ " መልካም አስተዳደር ማለት በአንድ አገር ሥልጣን ለዜጎች የጋራ ጥቅም ተግባራዊ የሚሆንባቸው ልምዶችና ተቋዋማት ማለት ነው።" የመልካም አስተዳደርን ዋና ዋና መርሆዎችና ባህርያትም በአሥር መለያዎች ይተነትኖአቸዋል። በእነዚህ መመዘኛዎች መሠረትም የመልካም አስተዳደር እጦት በኢትዮጵያ በገሀድ እንደሚታይና የችግሮቻችን ምንጭ እንደሆነ በመጽሀፉ ተብራርቶአል።

በምዕራፍ ሁለትና ሶስት ባለፉት 50 ዓመታት በኢትዮጵያ የነበሩት ሶስት አገዛዞችን አስከፊና አጥፊ ባህሪያት ገምግሞ በተለይም የወያኔ አስተዳደር ማለትም የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አመጣጥ እውነተኛ ባህርይና ይዘት ከለየለት አምባገነናዊ አገዛዝ ፈጽሞ ያልተለየ መሆኑን ለአንባቢያን በጥልቀት ይገልጻል። ምዕራፍ አራትና አምስት እንደዚሁ በሀገራችን ተንሰራፍቶ ስለሚገኘው ድህነት፤ ሶሻል ደህንነትና ስለ ሕዝባችን የጋራ ዓላማና የማህበራዊ ኑሮ ትሥሥር ሰፊ ትንታኔ ያቀርባሉ። በዚሁ ሥር የኢትዮጵያ የአእምሮ ፍልሰት ምን ያህል ሀገራችንና ወገኖቻችንን እንደጎዳ በዝርዝር ይገልጻል። ምዕራፍ ስድስት ሀገራችንን ከገጠማት አስከፊ ችግር አላቆ የወደፊት እድገትዋንና የሕዝቦችዋን ደህንነት በሁሉም አንፃር ለማስጠበቅ የሚያስፈልጋትን የፖለቲካና የሶሻል ተቁዋማት ይመረምራል። ምዕራፍ ሰባት በተለይም በውጭ ሀገር የምንኖረው የወገኖቻችንን ፍላጎት መሠረታዊ የዲሞክራቲክ መብቶቻቸው ተከብረው ያለፍርሀትና ያለሥጋት ኑሮአቸውን የሚመሩበትን ሁኔታ እንዲፈጠር ለመርዳት መጫወት ስላለብን ሚና በሰፊው ይዘረዝራል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በዚህ ርዕስ ላይ ማለትም በአንድ ሀገር መልካም አስተዳደር ይዘት በርካታ መጽሀፍቶችም ሆኑ የተለያዩ ሥነ ጽሁፎች ቢወጡም፤ ይህን መጽሐፍ የተለየ የሚያደርገው በሀገራችን የዲሞክራቲክ ንቅናቄ መሪዎች ብሎም በደጋፊዎች መሀከል በአሁኑ ወቅት የሚታየው ልዩነት በከፊል በዚህ መጽሐፍ በጥራት የተዘረዘሩትን ትምህርት አዘል እውነታዎች ባለመረዳት መሆኑን የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ይገነዘባል። አቶ ታምራት ስመኝ የህገራችንን ወቅታዊ የሶሽል የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግሮች ከነመፍትሄዎቻቸው በጥሩ ሁኔታ አቅርበውልናል። ከእኔ እውቀት በላይ ለአሳር ለሚሉ ወገኖች ሁሉ “ የዲሞክራሲ መሠረቶች በኢትዮጵያ” “የዓላማ አንድነት ለድል ወሳኝ ነው” የተሰኘውን መጽሐፍ በማንበብ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። በአሁኑ ወቅትም በተቃዋሚዎች አካባቢ የሚታየውን ልዩነት ሊያጠብ ወይንም ሊያሻሽል እንደሚችል አምናለሁ። ይህም ለዲሞክራቲክ ንቅናቄአችን ብሎም ለሕዝባችንና ለሀገራችን እድገት ወሳኝነት አለው።

በመጨረሻም መጽሐፉን አሳትመው በሚፈለግበት ጊዜ ላቀረቡልን ወንድማችን አቶ ታምራት ቢ ስመኝ በራሴና በአንባብዮች ስም ምሥጋነዬን አቀርባለሁ።

ሰለሽ ጥላሁን

ሰኔ 2008